# ወዝቦ

ድሮ በልጅነቴ፣
ሳታልፍብኝ ውዷ እያቴ፣
ለእማሆይ ገላዬ፣
ከማያልቀው ጥያቄዬ፦
የሰው ቁጣን አለሳልሳ "ወዝቦ ነው::" ስትል ብሰማት፣
"ወዝቦ ደሞ ምንድን ነው?" ብላት፣
ደካማ ሆና እማይደክማት፣
የምረባ ሰው መስያት፣
ስታስረዳኝ ካንጀቷ፣
እነህ ነበሩ ቃላቷ፦
"ወዝቦማ ማለት፦ ዶፍ የዝናብ ወፈፌ፣
ውርጅብኝ ያልታሰበ ለካፌ፣
እንደ አውሬ የሚያስሮጥ፣
አገር የሚያናውጥ፣
ደራሽ ወንዝ የሚንፏፏ፣
ሰላማዊ ዋናተኛን የሚያዳፋ፣
የረጋን ቤት ጣራ ፈንቅል፣
የመብረቅ ቅልቅል፣
በሁከት የሚያጓራ፣
በንቀት የሚመራ፣
ጨቅላ ሰብልን ወጊ፣
የደሃ አዝመራን ጠራጊ፣
ቲኒሽ ትልቅ ዘራፊ፣
ካለምርጫ አርጋፊ፣
ግን ጊዜያዊ፣
ውሸንፍሩ ቅፅበታዊ፣
የእግዚሃር ንጥሻ፣
የቁጣው መድረሻ፣
የታሪክ ጠባሳ፣
ውድመቱ እማይረሳ፣
ችግር አስተማሪ፣
ግድፈተ ማሕተም አኗሪ፣
ወዲያው ፀሐይ የሚያስወጣ፣
ሙቀት የሚያስመጣ፣
በማለፉ ደስታን ፈጣሪ፣
የአንድነት ፍቅርን አጠናካሪ፣
በተዳፋት በአገር እንደመጣ፣
ተዳፍቶ ከአገር እሚወጣ፥ ማለት ነው ሌላም አይደል ::"

January 28, 2012 ግርማ

http://wuyiyit.blogspot.com